# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

ፕሮግራም፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

ታህሳስ 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

- ዘመቻ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ምንጠራ ተጀመረ፤ የቲፒ፤የመቀሌና የዲላ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የትምህርት ማቆም አድማ አደረጉ፤

- አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ሰራተኞች የሚደርስባቸውን አስተዳደራዊ በደል በመቃወም የስራ ማቆም አድማ አደረጉ፤

- በጎንደር ክፍለ ሀገር መሬቶች ላይ የትግራይ ብሔረሰብ አባላትን የማስፈሩ ርምጃ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መመሪያ ተላለፈ

የወያኔ አረመኔ ቡድን በተለያዩ የስራ መስክ እና በተለያዩ የኢንቨስትመንት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የሀገሪቱ ዜጎችን በዘመቻ መልክ እያሰቃየ ባለበት በአሁኑ ሰዓት አሁን ደግሞ ዘመቻ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በሚል አዲስ አቅድ አውጥቶ እየተንቀሰቀሰ መሆኑ ተጋለጠ፡፡

የወያኔ ቡድን ለከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ይረዳው ዘንድ ለኮታ ማሙያ ብሎ በየክልሉና በየከተማው ደረጃቸውን ያልጠበቁና ትምህርት ቤት ሳይሆን መጋዘኖች አድርጎ በከፈታቸው ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ባሉ ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ ችግር እና ስቃይ እያደረሰባቸው መሆኑ ተጋልጦዋል::

ሰሞኑን በቲፒና በመቀሌ እንዲሁም በዲላ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል እና ወደር አልባ ግፍ እየተፈጸመባቸው ከመሆኑም በላይ በዚሁ ሳቢያ አንዳንድ ተማሪዎች በብስጭት እራሳቸውን እስከ ማጥፋት ደርሰዋል::

የቲፒ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትምህርት ከጀመሩ ሁለት ወራትን ያስቆጠሩ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ በቀን አንድ ግዜ ቁራሽ ዳቦ እና ከውሀ የቀጠነ ሽሮ ከማቅረባቸው ሌላ የሚሰጣቸው እንደሌለ የተረዱት ተማሪዎቹ ትምህርት ማቆም አድማ አድርገው እንደሰነበቱ ታውቆዋል::

የሚሰጣቸው ምግብ እጅግ ጥራት የሌለው ከመሆኑም በላይ ለህፃን ልጅ የማትበቃ መሆኑን በተደጋጋሚ ግዜ ለትምህርት ቤቱ አመራሮች በቃልና በፅሁፍ ቢያሳውቁም ምላሽ ባለማግኘታቸው ለአንድ ሳምንት የትምህርት ማቆም አድማ አድርገዋል::

በተደጋጋሚ ግዜ አቤቱታ የቀረበላቸው የዩኒቨርስቲው አመራሮች እኛ የተሰጠንን እና የቀረበልንን ብቻ ነው የምንሰጣችሁ እኛም ከአቅማችን በላይ ነው የሆነብን ሲሉ ምላሽ በመስጠታቸው ከተማሪዎች ስድብና ተቃውሞ አልፎም ጥቃት የተሰነዘረባቸው ሲሆን የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት ግን ለስራ ጉዳይ በሚል ወደ ኔዘርላንድ መጉዋዙም ታውቆዋል::

ከምግብ ችግር ሌላ የንፁህ ውሀ አቅርቦት ጠፍቶ በወንዝ ውሀ ለመጠቀም የተገደዱት እነዚሁ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ችግሩ ከነገ ዛሬ ይቀረፋል በማለት ለትምህርታቸው ትልቅ ትኩረት ሰጥተው የነበረ ቢሆንም ችግሩ ስር ሰድዶ ከቀን ወደ ቀን እየሰፋና እየያደገ በመምጣቱ ሊቋቋቁሙት ከሚችሉት በላይ ስለሆነባቸው አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰሚ ባለማግኘታቸው የትምህርት ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በተጨማሪ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች ወደ የቤተሰቦቻቸው መመለሳቸውንም ለማወቅ ተችሎዋል::

ቀን እና ሌሊት መሆኑ የማይለይበት ይሄው ወያኔ ሰራሽ ዩኒቨርስቲ በቀን በጠራራ የጅብ መንጋ በግቢው ውስጥ እየተግተለተለ ተማሪዎቹ ማደሪያ ቤት እና መማሪያ ክፍሎች ድረስ እየገባ ጥቃት እየሰነዘረ መሆኑን የሚያውቁት እነ መለስ ዜናዊ

በተማሪዎቹ ላይ የሚደርሰውን አደጋ ከምንም ሳይቆጥሩት እና ለማሻሻል ሳይሞክሩ ለፖለቲካ መጠቀሚያቸው ሲሆን በቢሊዮን ብር እያፈሰሱ መሆናቸው እጅግ አሳዛኝ እና የተማረ የሰው ኃይል እንደሚጠሉ ያረጋገጠ መሆኑን ተማሪዎቹ አጽንኦት ሰጥተው ገልፀዋል::

በዲላ ዩኒቨርስቲ ውስጥም የውሀ፤የምግብ፤የመኝታ እና ሌሎች ተዛማጅ ተመሳሳይ ችግሮች የተከሰቱበት ሲሆን በተለይ በሳምንት ሁለት ተማሪ የሚሞትበት ግቢ እንደሆነም ታውቆዋል::

የዲላ ዩኒቨርስቲ ሲሰራ ደን የነበረ ቦታ ላይ ሲሆን የተለያዩ የዱር አውሬዎች የነበሩበት እና ጊንጥና እባብ መፈልፈያ የነበረበት መሆኑን እያወቁ አንድም ጽዳት እና የመጥረግ ስራ ሳይሰሩበት ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ አምስት እና ከዚያም በታች መጋዘኖችን ሰርቶ ዩኒቨርስቲ ብሎ ስያሜ ማውጣቱና ማስተማር መጀመሩን የተቃወሙ በርካታ ምሁራኖች ለእስር የተዳረጉ ቢሆንም ወያኔ በጀመረው ሰው ጨራሽ ፖሊሲው ገፍቶበት በአሁኑ ሰዓት እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ወጣቶች እያለቁ መሆኑ ተገልጾዋል።

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ብቻ በዲላ ዩኒቨርስቲ አንድ የጅማ ተወላጅ ሴት ተማሪ እና ሌላ ከጎጃም የመጣ ተማሪ በአንድ ሳምንት ውስጥ ከትምህርት ገበታቸው ላይ የደረሱበት ጠፍተው ቢፈለጉ ባለመገኘታቸው ለጠፉት እና ከዚያም በፊት ላልተገኙት ተማሪዎች ተጠያቂው የዩኒቨርስቲው አመራሮች ከዚያም አልፎ የወያኔ ቡድን ነው በማለት ተቃውሞ በማሰማት ከገቢው አልፈው ወደ ከተማው ለመውጣት ሙከራ ቢያደርጉም የፌዴራል ፖሊስ በመድረሱ በድብደባ ሊያስቆማቸው እንደቻለ ተገልፆዋል።

ተማሪዎቹ ላነሱት ጥያቄ መፍትሔ ያልሰጡት የወያኔ ሹመኛ የዩኒቨርስቲው አመራሮች በምሬት ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት በሞከሩበት ወቅት ግን የፌዴራል ፖሊስ ጠርተው ተማሪዎቹን ከማስደብደባቸው በተጨማሪ የአመፁ አነሳሽ ናቸው በሚል ከመሀከላቸው ከ20 ተማሪዎች በላይ አፍሰው ወደ እስር ቤት የከተቱዋቸው መሆኑንና ለአምስት ቀናት አንድም ሰው እንዳያገኛቸው ተደርገው በጭለማ ቤት ውስጥ እንዳከረሙዋቸውም ታውቆዋል።

በቅርቡ የውጭ ጉዳይና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ተሰጠው የተባለው የ ኃይለማርያም ደሳለኝ ታናሽ ወንድም የዲላ ዩኒቨርስቲ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆኖ የተሾመ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ይህ ግለሰብ ልክ ወንድሙ በሲዳማ ህዝብ ላይ እንዳደረሰው ጭፍጨፋና ዘግናኝ እልቂት ሁሉ እሱም በዲላ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ወደር የለሽ ግፍ በፌዴራል ፖሊስ እንዲፈጸምባቸው ትዕዛዝ መስጠቱ ተረጋግጦዋል።

በዕለቱ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ወንድ ተማሪዎች ብልታቸውን ሴት ተማሪዎች ማህጸናቸውን በጥቁር ዱላ ሆን ብለው የቀጠቀጡዋቸው በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ሆስፒታል ተኝተው በህክምና ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ ግማሾቹን ቤተሰቦቻቸው መጥተው የተሻለ ህክምና ወደሚያገኙበት እንደወሰዱዋቸው ለማወቅ ተችሎዋል።

የዲላ ዩኒቨርስቲ በሁለት ግቢ ተከፍሎ የተሰራ ከመሆኑም በላይ ጥልቀቱ እጅግ እረዥም የሆነ ጥቁር ወንዝ መሀል ለመሀል ቆርጦ የሚያልፍ ሲሆን በግቢው የተለያዩ የዱር አውሬዎች ያሉበት በመሆኑ ከአንደኛው ግቢ ወደ ሌላኛው ግቢ ለማለፍ በቡድን ካልሆኑ በስተቀር በተናጠል መንቀሳቀስ የማይቻል በመሆኑ ተማሪዎቹ በፍርሀት ተውጠው በግዴታ እየተማሩ መሆኑም ተረጋግጦዋል።

በግቢው መሀል ቆርጦ የሚያልፈው ወንዝ የተበላሸና መልኩን የቀየረ ከመሆኑም በተጨማሪ ሽታ ያለው በመሆኑ ብዙ ተማሪዎች በበሽታ እየተጠቁ እራሳቸውን እስከ መሳት የደረሱ ሲሆን በመኖሪያ

ክፍሎቻቸው ውስጥም የእባብ መንጋ እየገባ ጥቃት እያደረሰባቸው ሲሆን በቅርቡም አንድ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ በእባብ ተነድፋ ህይወትዋ ሊያልፍ ችሎዋል፡፡

በተማሪዎቹ ላይ ይህን የመሰለና የከፋ ችግር እየደረሰባቸው ከመሆኑም ባሻገር የውሀ እና የምግብ አቅርቦት ዜሮ ከመሆኑም በላይ ለሴት ተማሪዎች ምቹ የሆነ የሽንት ቤት መጠቀሚያ አጥተው ወደ ከተማ ሄደው በህዝብ ሽንት ቤት ለመጠቀም እንደተገደዱም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ቤተሰቦቻቸው አቅም ያላቸው አንዳንድ የዲላ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በከተማው መሀል ቤት ተከራይተውላቸው የሚያስተምሩዋቸው ቢሆንም ግቢ ሲገቡና ሲወጡ እባብና ጊንጥ በመኖሩ በፍርሀት እየተመለሱ በትምህርት ገበታቸው ላይ ከሚገኙበት የማይገኙበት እየበለጠ እንደመጣም ታውቆዋል፡፡በዚህም የተነሳ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች ውጤታቸው ደካማ ሊሆን እንደቻለና ለብዙዎቹ መባረር ምክንያት ሆኖዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በዲላና በቲፒ ዩኒቨርሰቲዎች ውስጥ የተከሰተው ችግር በተመሳሳይ መልኩ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ላይ ችግሩ ተከስቶ እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ፡፡

ወያኔ እራሱ ያወጣውን የወጪ መጋራት ደንብ እየጣሰ ተማሪዎቹን በርሀብ እና በመኝታ እየቀጣቸው ከመሆኑም በላይ ለከፋ ችግር ዳርጎዋቸው እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ተማሪዎቹ ተመርቀው ስራ ሲይዙ የሚከፍሉት እዳ መሆኑ እየታወቀ እስከ አሁን ድረስ ለ3 ወራት ያህል ገንዘብ ያልተከፈላቸው በመሆኑ ምግብ እና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን መሸፈን ባለመቻላቸው ከአለፈው ሳምንት ጀምሮ ትምህርት ለማቆም እንደተገደዱ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ ገልፆ የዩኒቨርስቲው አመራሮች ለተማሪዎቹ ጥያቄ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ለፖለቲካው ትልቅ ትኩረት ሰጥተው እንደሚገኙም ታውቆዋል፡፡

ትምህርት ከጀመሩ ሶስት ወራቶችን ያስቆጠሩ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ አንዳችም ወጪ ከዩኒቨርስቲው ያልተሰጣቸው በመሆኑ ለከፋ ርሀብ እንደተዳረጉና ትምህርታቸውን ለማቆም እንደሚገደዱ በተደጋጋሚ ለአመራሮቹ ቢነግሩም ምላሽ በማጣታቸው በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ የትምህርት ማቆም አድማ እንደሚያደርጉ በገለጹት መሰረት ባለፈው ሳምንት ትምህርት ማቆማቸው ታውቆዋል፡፡

ተማሪዎቹ በወሰዱት የትምህርት ማቆም አድማ እርምጃ የተበሳጨት የወያኔ ካድሬ የዩኒቨርስቲው አመራሮች አድማውን ያንቀሳቀሱና ያቀጣጠሉ ናቸው በሚል ከ30 በላይ ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው ላይ የሚያግድ ደብዳቤ እንደተሰጣቸው እና ዘንድሮ መማር እንደማይችሉ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በተለይ በጉዳዩ ላይ እጅግ የተበሳጨ አምስት ከአዲስ አበባ የመጡ ሴት ተማሪዎች እያለቀሱ ከእንግዲህ የመንግስት ዩኒቨርስቲ ውስጥ ገብተን አንማርም በማለት ቤተሰቦቻቸው ወደሚገኙበት አዲስ አበባ ጉዋደኞቻቸውን ተሰናብተው መሔዳቸው ከመቀሌ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በሌላ ዜና አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ሰራተኞች የሚደርስባቸውን አስተዳደራዊ በደል በመቃወም ለሁለት ቀናት የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደነበር ታወቀ::

ባለፈው ሳምንት ሐሙስ እና ዓርብ ህዳር 24 እና 25 ቀን 2003 ዓ.ም ለሁለት ተከታታይ ቀናት ሙሉ ለሙሉ ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ አድርገው የሰነበቱ ሲሆን ሌሎች ሰራተኞችም እነሱን ተከትለው አድማውን ተቀላቅለው እንደነበር ታውቆዋል::

ከአንድ ሺ በላይ ሹፌሮች እና መካኒኮች በአድማው ላይ የተሳተፉ ሲሆን የአድማው ዋና አላማ ወያኔ የሾማቸው የድርጅቱ አመራሮች በሹፌሮቹ እና በሰራተኞች ላይ ጥብቅ ደንብ በማውጣታቸው መሆኑ ታውቆዋል::

በሚያሽከረክሩበት ወቅት በግጭት ምክንያት ለሚወድመው ንብረት ተጠያቂው ሹፌሩ ነው በሚል አሳሪና የማያላውስ ደንብ አውጥተው በመግለጻቸው የተናደዱት እና የተበሳጩት ሹፌሮች የያዙትን አውቶቡሶች በያሉበት ገትረው ለሁለት ቀናት የስራ ማቆም አድማ ያደረጉ ሲሆን እነሱን ተከትሎ መካኒኮችም የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደነበር ለመረዳት ተችሎዋል::

ከ30 ዓመት በላይ ስናሽከረክር የረባ የደመወዝ ጭማሪ ሳታደርጉና የተሻለ ምቹ ሁኔታ ሳትፈጥሩ በእኛ ላይ ግዴታ መጣላችሁ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ድርጅቱ የተሙዋላ ኢንሹራንስ እያለው እኛን ባለእዳ ለማድረግ መሽቀዳደማችሁ የሚያሳፍር ነው በማለት መኪኖቻቸውን ቆላልፈው ለሁለት ቀናት የስራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው የተደናገጡት የወያኔ ካድሬ ሹመኞች ደብዳቤውን ለማንሳት እና ደንቡንም ለመሰረዝ እንደተገደዱ ለመዋቅ ተችሎዋል::

በወያኔ ካድሬ ሹመኞች  የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲነሳ ተደርጎ ስራ የጀመሩት ሹፌሮች እና መካኒኮች ላይ ውስጥ ውስጡን አቁዋም ያስያዙ ናቸው የሚባሉትን ሰራተኞች በተለያዩ የተንኮል ወጥመድ ጠልፎ ለመጣል ሴራ እየተሴረ መሆኑንም ከሰራተኞቹ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በዚህም ሴራ ዋነኛ ተዋናዮች እና ለስለላ ስራው ይረዳቸው ዘንድ በትኬት ቆራጭነት የተቀጠሩት እና እየሰሩ ያሉት የወያኔ የወጣት ፎረም አባሎች መሆናቸውን  የደረሰን ጥቆማ ገልፆ ሹፌሮቹ በሚሰሩበት ቦታና በእረፍት ግዜያቸው ሁሉ ክትትል እንደሚደረግባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

በአሁኑ ወቅት ለትኬት ቆራጭነት የሚቀጠሩት ወጣት ሴት እና ወንድ የፎረም አባሎች ብቻ ሲሆኑ እነሱም ለስለላ ስራ ተብለው የ15 ቀናት ኮርስ እንደሚሰጣቸውና ቀኑን ሙሉ ከህዝቡ ጋር ስለሚገናኙ እየተከታተሉ ማታ ማታ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ለመረዳት ተችሎዋል::

የኢትዮጵያ የወርቅ ሀብት በአላሙዲና ኣዜብ ጎላ ማለትም የመለስ ሚስት እጅ ገብቶ ለሀገር ምንም ጥቅም የማይሰጥ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ሀገርን ለባዕድ በመሸጥ ላይ ያለው የመለስ አገዛዝ በትግራይ ይኖራል የሚባለውን ወደ 500 ቶን ማለትም 500ሺ ኪሎግራም የወርቅ ክምችት ፍለጋ ሺባ ለሚባል የእንግሊዝ ሀገር ኩባንያ መስጠቱ ተዘገበ። ባለፈው ዓመት ከወርቅ ሽያጭ ከ 300 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ ሲባል ከዚህ ገንዘብ አብዛኛው በወያኔ  እጅ መግባቱ ታውቋል። በመለስ አገዛዝ ፍቃድ ተሰጥቷቸው በኢትዮጵያ ማዕድን ፍለጋ የተሰማሩ 86 ኩባንያዎች ሲኖሩ 30ዎቹ ወርቅ ወደ ውጭ እያልኩ ያልሉ ናቸው ተብሏል። ከወርቅ ሌላ ብዙ የማዕድን ምርቶችም ወደ ውጭ ሀገር እየተሸጡ ገቢውም ወደነ መለስ ኪስ እየገባ ነው ተብሏል። በሻኪሶ ሲመረት ይባጀውም ወርቅ ገቢ በአላሙዲና መለስ መሀል ተከፋፍሎ ቀሪ መሆኑም ቀደም የተጋለጠ ጉዳይ ነው። በተያያዘ ዜና ኤርትራም የወርቅ ክምችት እያገኘች ናትና በዚህ ትርፍ ኢሳያስ  ከመክበሩ በፊት ማስወገድ ያስፈልጋል በሚል የመለስ አገዛዝ እየተወራጨ መሆኑን አንዳንድ የዜና ምንጮች ይገልጻሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ ሰሞኑን መቀመጫውን ኤርትራ አድርጓል የተባለው የአርበኞች ግንባር የአንድ ወቅት መሪ የነበረው ኮለኔል ታደሰ ሙሉነህ ኣስመራ ከተማ በሻዕቢያ በጸጥታ ፖሊሶች ተይዞ መዳረሻው ጠፋ የሚል ዜና ተሰራጭቷል።

የመለስ ቡድን በቅርቡ ባስተላለፈው የምስጢር መመሪያ ወደ ትግራይ በተጠቃለሉት የጎንደር መሬቶች የትግራይ ተወላጆችን የማስፈሩ እርምጃ ብቂ አለመሆኑን ጠቅሶ የማስፈሩ እርምጃ እንዲጣደፍ ዕዝ አስተላፏል። ታዛቢዎች በሁመራና ኣብደራፊ ለምሳሌ ከ 90 በመቶ በላይ ነዋሪው የትግራይ ተወላጅ ሆኗል የሚሉ ሲሆን ወያኔ ግን ይህ በቂ ሆኖ ያገኘው አልሆነም። መመሪያው ለሰፋሪዎች ድጋፍና እገዛም እንዲሰጣቸው አዟል። በንዚህ አካባቢዎች አመራር በሚል ለ ጭቆና የተዳረገው ሕዝብ ደግሞ ታዳጊ አጥቶ በመሰቃየት ላይ መሆኑ ተነግሯል። የሰፈራው ዕዝ ወሎንም የሚመለከት መሆኑም ታውቋል። ዘረኛው የመለስ ቡድን የትግራይ ተወላጆችን በጎንደርና ወሎ በ ማስፈር መሬቱ የትግራይ ነው ለሚለው ሽፍጡ ማጠየቂያ እያዘጋጀ መሆኑ የሚታይ ነው። ከዚሁ በተያያዘ መለስን ተቃወምን ብለው ከድርጅቱ የወጡት የውያነ የቀድሞ መሪዎች ይህን የወያኔን የመሬት ቅሚያ ሲያወግዙ እስካሁን ኣለመደመጣቸውም ተገልጧል። በተለይም በወልቃይት፡ ጠገዴ፤ ጸለምት ህግረው ብዙ መከራ እያየ መሆኑ በተደጋጋሚ ተዘግቧል።